"የአሲምባ ፍቅር"

ደራሲ፡ ካሕሳይ አብርሃ

አስተያየት፡ ጸሐየ ሰለሞን ኅዳር 13 ቀን 2006 ዓ.ም.

በቅርብ ጊዜ "የአሲምባ ፍቅር" በሚል ርዕስ ባጠቃላይ የዛን ትውልድ ገድል፣ በተለይ ግን የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ሠራዊትን (ኢሕአሠ) ታሪክ በጊዜው በነበረ ተሳታፊ እይታ የተፃፈ እውነተኛ ታሪክ ምንባብ በመጽሐፍ መልክ ለገበያ ወጥቷል። ደራሲ ካሕሳይ አብርሃ፣ በሜዳ ስሙ አማኑኤል፣ ጊዜውን ከልጆቹና ከባለቤቱ ተቀራምቶ ይህን መጽሐፍ ስላቀረበልን በቅድሚያ ላመሰግነው እፈልጋለሁ።

በደፈናው እስካሁን ድረስ የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ)ን ታሪክና ተጋድሎውን የሚመለከቱ መጻሕፍት ሲወጡ ማየት በጣም ያስደስተኛል። ያ ጀግንነት፣ ያ ቆራጥነት፣ ያ ለሰፊው ሕዝብ መቆም፣ ያ ለኢትዮጵያ የግዛት አንድነትና ሉዓላዊነት ሲባል ያለ ምንም ማመንታት ህይወታቸውን ከምንም ሳይቆጥሩ ለሰፊው የኢትዮጵያ ህዝብ ቤዛ ለሆኑና ዓላማቸውን ከግብ ለማድረስ የተደረገ ትግልና የተከፈለ መስዋእትነት ለታሪክ መጻፍ አለበት። መዘገብ አለበት። ይህ ሲባል ግን የተዛባ፣ በቅጡ ያልተዘገበ ነገር/ጉዳይ መጻፍ አለበት ማለት አይደለም። ጸሐፊዎቹ የሚጽፉት፣ የሰማዕታት ታሪክ መሆኑን ላንዴም ቢሆን መዘንጋት የለባቸውም። የሚጽፉት የራሳቸውን ታሪክ ብቻ አይደለም። ያለ ተሰዉት ጓዶቻቸውና ኢሕአፓ/ኢሕአሠ የነሱ የትግል ታሪክ የለምና።

ይህን ካልኩ በኋላ ይህን መጣጥፍ እንድሞጫጭር ወደ አነሳሱኝ ጉድዮች ላይ ልመለስ። "የአሲምባ ፍቅር" መጽሐፍ ገበያ ላይ መውጣት በኋላ፤ ከአንባቢያን ከተለያዩ አቅጣጫዎች የተሰነዘሩ አስተያየቶች፣ ትችቶችና አቃቂሮች አንብቤአለሁ። አንዳንዶቹ ተገቢ የሆነ ገንቢ ሀሳቦችንና ግድፈቶችን ሲያሳዩ፣ አንዳንዶቹ ደግሞ ግምት ላይ የተመሰረተ ድምድሜ ላይም ገብተዋል። በኔ ግምት ከተነሱት አንዳንድ ነጥቦች መሃል ትልቅ ስህተትና ግድፈት በሚመስሉኝ ነጥቦች ላይ ሳተኩር ከሁሉም በላይ ግን ትልቅ ስህተት ነው የምለው፤ በአንዳንድ ተቺዎች በትግራይ ልጆች ላይ የተሰነዘረው አስተያየት ነው።

በጭብጥ ደረጃ፣ ኢሕአፓ/ኢሕአሠን፣ አሁን ድረስ ከሌሎች ድርጅቶች ልዩ የሚያደርገው ነገር ቢኖርና ጥንካሬው፣ እውነት ለእውነት ህብረ-ብሔራዊ ድርጅት መሆኑ ነው። አባላቶቹ ከሰሜን ኤርትራ ከሚመጡት ቢለኖች ጀምሮ እስከ የኢትዮጵያ ደቡባዊ ጠረፍ ከሚገኙት የቦረና ተወላጆች ድረስ ሲሄድ በመሃል ከሚገኙት ሁሉም ብሔሮች የተውጣጣ ነበር። ላንዳንዶቻችን፣ መኖራቸውን ጭራሽ ከማናውቃቸው አናሳ ብሔረሰቦች ጋር ያስተዋወቀን ኢሕአሠ ነበር። ኢሕአፓ/ኢሕአሠ ኢትዮጵያ ነበር። በስሙም ላይ ሕዝባዊ እንዳለው መለያው ኢትዮጵያዊነት ነው። ይህ ነው ኢሕአፓ፣ ይህ ነው ኢሕአሠ። ኢሕአፓ/ኢሕአሠ የተለያዩ ብሔር/ብሔረሰቦችን ማቀፍ ብቻ ሳይሆን ብሔራዊ ማንነትን ያሳየ፣ ያስተማረ ፓርቲ/ሠራዊት ነው። የኢሕአፓ ልጆች በደማቸው ኢትዮጵያዊነትን አለምልመዋል። በኢትዮጵያ የፖለቲካ ትግል ታሪክ ዘርን ሳይለይ፣ በክልል ሳይወሰን ሁሉን አቅፎ ለሀገርና ለሕዝብ ያሰለፈ የመጀመሪያ ፓርቲ፣ ፆታ ሳይለይ ሴቶች እህቶቻችንን አሰልፎ የትግሉ እመቤትነታቸውን ያስመሰከረ፣ ሃይማኖት ሳይገድበው ሙስሊሙን ከክርስቲያኑ አስተቃቅፎ ያሰለፈ ብቸኛና ቀዳሚ ፓርቲ ኢሕአፓ ነው።

የኢሕአፓ ሕብረ ብሔራዊነቱ፣ ሕዝባዊነቱ እንደተጠበቀ ሆኖ፤ የሰራዊቱን መስራች አስኳል መጀመሪያ ላይ ተቀላቅለው ያጎለበቱት፣ ወታደራዊ ጥንካሬ በቅድሚያ የሰጡት የትግራይ ልጆች በርካታ ነበሩ ቢባል ማጋነን አይደለም። በመሆኑም፣ ፓርቲው በከተማ ከፍተኛ ጥቃት ደርሶበት፣ በርካታ አባላት ወደ ሠራዊቱ ተቀላቅለው መልኩን ከቀየሩት በኋላ እንኳን የሰራዊቱን ወታደራዊ አመራር ቀጥ አድርገው የያዙት አሁንም

በአብዛኛው የትግራይ ልጆች ነበሩ። በከፍተኛ ደረጃም መስዋእትነት የከፈሉት የትግራይ ልጆች ነበሩ። ዘር መቁጠር አይሁንና በኢሕአፓ ጥላ ሥር የትግራይ ልጆች ደም ደቡብ ፈሷል፣ የወላይታ አጥንት ሰሜን ተከስክሷል፣ የኦሮሞ ልጆች ከሊማሊሞ ገደል ተወርውረዋል፣ የጉራጌ ልጆች አሲምባ አሸልበዋል፣ ወዘተ። ሁሉም ለሀገሩ ክብርና ለሕዝቡ መብት በኢሕአፓ ጥላ ሥር በየትኛውም የሀገሪቷ ክልል ታግሏል፤ ተዋድቋል። ከተለያየ ብሔር/ብሔረሰብ ይምጡ እንጂ የጋራ ቋንቋቸው ኢትዮጵያ ናት። የትግላቸው መፈክር የዴሞክራሲ መብት ነው፤ ጥያቄያቸው ለሕዝብ የሕዝብ መንግስት ነው። ይህ ነው ዝማሬአቸው፤ ይህ ነው የጋራ ጩኸታቸው። ብሔራዊ ኩራታቸው፤ ኢትዮጵያዊ አንድነታቸው።

ዛሬ ጊዜ ጉልበት እሆነው ዘረኝነት ላይ ቆመን፤ የትግራይ ልጆች የወያኔ ተባባሪዎች እንደነበሩ አድርጎ ማቅረብ፣ ታሪክን ማጉደፍ፣ በቆራጥነትና በጀግንነት የተሰዉ አባላትን ደም ከንቱ ማድረግ ይሆናል። ዛሬ የወያኔ/ህወሓት አዳማቂዎች ኢሕአፓ/ኢሕአሠ ውስጥ የነበሩም ነበሩበት ብለን የትግራይ ልጆች አድፍጠው የነበሩ ዘረኞች አድርጎ መውሰድ በሰማዕታት ወገኖቻችን ላይ ማሾፍ ይሆናል። ይህን ዓይነት ከፍተኛ ግድፈት የፈጸሙ የድሮ አባላትን ዝም ማለት ውቅሮ ከደርግ ሥራዊት ጋር ሲፋለም ያደገባት ከተማና ቤቱ በር ላይ የተሰዋውን የኃይል መሪ፣ የጓድ ያዕብዮን ጀግንነት፣ እስከ መጨረሻ ከወያኔ ጋር ሲፋለም የተሰዋው፣ የሠራዊት ከፍተኛ አመራር አባል የነበረውን የአያ በርሄን ልባምነትና ቆራጥነት፣ በጎጃም፣ ቤኒሻንጉል አካባቢ ከወያኔ ጋር ሲዋጋ የተሰዋውን የቢለን ተወላጁና የሠራዊቱ አመራር አባል የነበረውን የጓድ ጃብርን ቅንነትና ታታሪነት፣ ከተወለደበት ዓሲምባ ሰራዊቱን ተቀላቅሎ የሠራዊቱ የመረጃ (ኢንተለጀንስ) ክፍል መሪ የነበረው፣ በኋላም የሠራዊቱ ከፍተኛ አመራር አባል የነበረውና በምዕራብ በጌምድር የተሰዋው የጀግናው የጓድ ሓድሽ በየነን ሕይወትና ጀግንነት ማጉደፍና ማንቋሸሽ ይሆናል። ሁሉም፣ ከላይ የተጠቀሱትና ሌሎችም ለድርጅቱ የነበራቸው ፍቅርና ታማኝነት ወደር የሌለው እንደነበረ ሊካድ የማይችል ሃቅ ነው።

ከላይ የተጠቀሰውን ወቀሳ ላነሱ ሰዎች ፈጽመው ያልተገነዘቡት አንድ ሌላ ጭብጥም አለ። እሱም ኢሕአፓንና ኢሕአሠን የተቀላቀሉ የትግራይ የኤርትራ ልጆች ጥንካሪያቸውንና ኢትዮጵያዊነታቸውን የሚያመላክት ሌላም ገጽታ እንዳለ እንዲያዩ እፈልጋለሁ። መንግሥት ለመጨበጥ በሩ ላይ ደርሰው የነበሩ ጀብሃና ሻዕቢያ የመሰሉ ድርጅቶች፣ እንዲሁም ወያኔ የመሰሉ አማራጭ ድርጅቶች ነበሯቸው። በትውልዳቸው እነዚህ ድርጅቶች ውስጥ ተቀላቅለው ሊታገሉ ይችሉ ነበር፤ ግን አላደረጉትም። ጭራሹንም ከሌሎቹ ድርጅቶች በላይ አሕአፓንና ኢሕአሠን መርጠው ነው የታገሉት። በተፈጥሯዊ አጋጣሚ ከኤርትራና ትግራይ ውጭ የተወለዱት፣ ሌላም ብዙ ምርጫ አልነበራቸውም፣ እንደ ምርጫ ደርግን ካስቀመጥን፣ አሰላለፉ የተለየ ይሆንና በጠላትነት ተፈራርጀን እንፈላለም ነበር ማለት ነው። ይህ ራሱ፣ የጓዶቹን ቆራጥነት፣ ኢሕአፓነት፣ ኢትዮጵያዊነት ቁልጭ አድርጎ የሚያሳይ ማስረጃ ነው።

ለኢሕአፓ/ኢሕአሠ እንኳን የትግራይ ልጆች የትግራይ ሕዝብ ዋልታ መከታው ነበር። ዐባይ ኢትዮጵያ ሲልም፣ ወያኔና እነሻዕቢያ አሉታዊ ትርጉም ሊሰጡት ቢሞክሩም፣ ለህዝቡ ግን ለኢትዮጵያ ላለው ፍቅር ስያሜ ነበር። የፓርቲውና የሠራዊቱ ከዓሲምባ መልቀቅ ታሪኩን ለማዛባት ካልሆነ በቀር፣ ፍጹም ነው እምነቱ ብለው በዓሲምባ በረሃ የተኙ የትግራይ ልጆችን ለመቀስቀስ ካልሆነ በቀር ሚዛን አይደፋም። የኢሕአሠ ከዓሲምባ መውጣት በአጠቃላይ ኢሕአፓ በከተማም ሆነ በሌሎች አካባቢዎች ከደረሰበት ጥቃት ተነጥሎ አይታይም። ታሪኩ ተያያዥነትና ተወራራሽነት ይኖረዋልና።

የመጽሐፉን ሌላ መልክ ስመለከት፣ በካሕሳይ አብርሃ በኩል የታዩኝን ግድፈቶች ከዚህ ቀጥየ ማሳየት እፈልጋለሁ። አንድ ትልቅ ስህተት የሚመስለኝ፣ በድርጅቱ/ሠራዊቱ ሕይወት ላይ ምንም ተጽእኖ የሌላቸውን ጉዳዮች በማንሳት ራሳቸውን ሊከላከሉ የማይችሉ የተሰዉ ጓዶችን ስም ማካተቱ ነው። ጓድ አበበ

ደብተራውና ጓዲት ድላይ በምንም ዓይነት መልክ፣ ከቆራጥነታቸውና ከጀግንነታቸው በመለስ በተነሱበት መልክ መነሳቱ ትልቅ ግድፈት ነው።

በሁለተኛ ደረጃ መነሳት ያለበት ጉዳይ የውቅሮን ወታደራዊ እርምጃን በሚመለከት ያሰፈረው ነው። እንደ አማኑኤል አባባል፣ ፍሱሕ ረዳኢና እሱ ራሱ የከተማ ጓዶችን አግኝተው አዲስ መረጃ እንዲያመጡ በነበረው የኦፕሬሽኑ አመራሮች ይታዘዛሉ። በተባለውም መሰረት ሄደው የከተማ ጓዶችን ያገኛሉ። ከከተማ ጓዶች እንደተረዱት ውቅሮ ውስጥ የተለወጠ ወታደራዊ ሁኔታ እንዳለ ይነገራቸዋል። እንደ አማኑኤል አጻጻፍ ረዳኢ ይህን አዲስ ተለዋጭ ሁኔታ በሚስጢር እንዲያዝ ይነግራቸዋል። ለዚህ ተልእኮ ሙሉ ኃላፊነት ተሰጥቷቸው አመራር የነበሩት ጓድ ወርቁ፣ ጓድ ሰለሞን እንዲሁም የሃይል መሪዎቹ፣ ጓዶች ያዕብዮና ህብስቱ ነበሩ። ይህ ተልእኮውን ያከሸፈ አዲስ ተለዋጭ ሁኔታ ለአመራሩ ሳይናገሩ በሚስጥር የያዙት ጓዶች በምን ደረጃ ላስቀምጠው እንደምችል የማላውቀው ትልቅ ስህተት ፈጽመዋል። በመጽሓፉ ውስጥ ካሕሳይ (አማኑኤል) የዚህን ስህተት ተንትኖ በሚገባ ማስቀመጥ ሲገባው፣ እንዲሁ ባጭሩ ጠቀስ አድርጎ ማለፉ ትልቅ ግድፈት ነው።

የኢሕአፓ ታሪክ በአንድ መጽሐፍ የሚጠቃለል አይደለም። በትግሉ መላ ሀገሪቷን እንዳዳረሰና እንዳንቀሳቀሰ በየአካባቢው ያለው እንቅስቃሴ እራሱ ከኢሕአፓ ጋር ይያያዛል። በየቦታው ያሉ በርካታ እስር ቤቶች ታሪክ ኢሕአፓን ይዳስሣል። የተማሪዎች፣ የሴቶች፤ የጭቁን ወታደሮች፣ የእናቶች፣ የሠራተኛው ማህበር፣ የመምህራን ማህበር፣ የወጣቶች (ኢሕአወሊ) ወዘተ ታሪክ ሁላ መች ተነካና። ሁሉም የሚያውቀውንና የሚችለውን ቢጽፍ አሁንም ይመረጣል። ችሎታውና ዕውቀቱ ያላቸው ግለሰቦች የሚያውቁትን ታሪክ ሳያዛቡ ለንባብ ማብቃት ጠቀሜታው የጎላ በመሆኑ መበረታታት አለበት እላለሁ። ፀሀፊዎችም የሚሰጣችሁን አግባብ ያለው ትችት ለመቀበል ብቃቱ ይኖራቸው ዘንድ ይጠበቃል። ጽፋችሁ ለንባብ ለምታቀርቡት መጽሐፍ በተለይ ዕውነተኛ ታሪክ ተብሎ ለሚቀርበው ከፍተኛ ጥንቃቄን ማድረግ ይጠበቅባችኋል። አሁንም በተለይ የታሪኩ የመጀመሪያ ተጋሪዎች በቀሪ ዕድሚያችሁ የምትችሉትን ፃፉና አስነብቡን፤ ለትውልድና ለሀገርም ታሪኩን አስቀምጡ::

በመጨረሻ ልለው የምፈልግ ነገር ቢኖር በካሕሣይ አብርሃና በአንዳንድ ተቺዎች መካከል በተደረገው ምልልስ የተጠቀሙባቸው ቃላቶች አግባብ እንዳልሆኑና ከጓድነታዊ ስሜት የራቁ መሆናቸውን ነው። ተገቢ አይደለም። ኢሕአፓንና ኢሕአሠን በሚመለከት ገና ብዙ መጻሕፍት ሊታተሙ እንደሆነ መገመት አዳጋች አይሆንም። የድርጅታችንን ምንነትና የጓዶቻችንን ጀግንነት የሚፈታተኑ ሌሎች ጽሑፎች እንደሚወጡም ማወቅ ይኖርብናል። ባንዳንድ አመለካከቶችና ትንተና በተላያየን ቁጥር፣ አሁን ባየነው መልክ ከተመላለስን፣ የተሰዉ ጓዶቻችንን ታሪክ ማጉደፍ እንደሚሆን ካሁኑ ማወቅ ይኖርብናል። ይህ ዓይነት ባህሪ ፈጽሞ መወገድ ይኖርበታል።

የጀግኖቻችን መንፈስ በሁላችንም ይስፈር!!!